# በሎስ አንጀለስና አካባቢውየምንገኝ አገር ወዳድ ሰደተኛ ኢትዮጵያዊያን ግብር ኃይል

## አልሞትኩም ብዬ አልዋሺም

- በሀገራችን የፖለቲካ ሁኔታ ወያኔ ከመቸውም ጊዜ በላይ በራሱ ጥቂት የበላይ ጠባቂዎች ለድርጎ ያደሩ ተጠቃሚዎችና በየቢሮክራሲው የተሰገሰጉ ግለሰቦች በስተቀር እተማመንበታለሁ ከሚለው የትግራይ አካባቢ እንኳን እየተነጠለ ያለበት ሁኔታ ላይ ነው ያለው።
- ኢኮኖሚው ዳሺቆ፤ የውጭ ምንዛሬው መንምኖ፤ የዋጋ ግሽበት ወደ ላይ መጋለቡን ቀጥሏል። ከውጪ አየር ባየር በርካሺ የሚገቡና ገቢያውን የሚያጨናንቁ እቃዎች፤ በሀገር ውስጥ ተመሳሳይ እቃዎችን በሚያመርቱ ትናንሽ ኢንዱስትሪዎች ላይ ከፍተኛ ጉዳት



እያደረሰ ነው። በርካታ ሰራተኞችም ከስራ እንዲባረሩ ምክንያት ሆኗል።
- ወያኔ የማይገባበት የኢኮኖሚ ዘርፍ



የለም። ከቀረጥ ነጻ በማስገባት ፤ የተሻለ የባንክ ብድር በማገኘት፤ በኤፈርት አማካይነት ካፒታሉን በማንቀሳቀስ ፤ ሌሎች ነጋዴዎች ላይ የልተመጣጠነ ግብር በመጣልና፤ ያልሆነ ምክንያት ፈልጎ ጫና በማድረግ የተሻለውን ገቢያ እየያዘ ነጋዴውን እየገድለው እንደሆነ በግልጽ የሚታዮ እውነት ነው፡፡
- ለም የእርሻ መሬት ለውጪ የመሬት ዘራፊዎች አሳልፎ በመስጠት የሚያደርገው እንቅሳቃሴ እየቀጠለ ነው። ከመሬታቸው የተፈናቀሉ ገበሬዎችና በነዚህ በውጭ ባለሀብቶች በተያዙት እርሻዎችም ላይ በዝቅተኛ ክፍያ ጭሰኛ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ለወያኔ ለውጪ ምንዛሬው አንዱ ምንጩ ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊው መሆኑ የታወቀ ነው። ወያኔ በሀገር ውስጥ ሁኔታው ሲጨልምበት በውጭ የሚገኘውን ዜጋ በፖለቲካውና በኤኮኖሚው ልቡን ለመሥለብ ታላቅ ሩጫ እያደረገ ነው። ብዙ ዲያስፖራውን የሚያማልሉ እንደ ልዩ መታወቂያ፤ መሬትና ቤትን በቀላሉ ሰላምገኘት፤ የኢንቨስትመንት ሂደቱን በተፋጠነ ለማስኬድ እንዲችሉና የመሳሠሉ ነገሮችን እየቀያየረ (ለውሻ አጥንት እድሚጣል አይነት) በማቅረብ ገንዝብ ለመዝረፍ በቻለው ሁሉ ድፋ ቀና እያለ ነው።
- ወያኔ ህዝቡ እሴቱን፤ አንድነቱንና ፍቅሩን ጠብቆ የሚሄድባቸውን ተቋማት ለመሸርሸር የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል፤ አድርጓልም። የትምህርት አሰጣጡ ደረጃ ምን ያህል ውድቅ መሆኑ የአደባባይ ሚስጥር ነው። የትምህርት እድል ያገኘው ደግሞ የስራ እድሉ የጠበበ ስለሆነ ሁሉ ነገር እየጨለመበት ወደ ውጭ መውጣት ብቻ እንዲታየው ተደርጓል። ችጋሩ ሲጠናበት “ሥራ” ፍለጋ በሚል ወደ መካክለኛው ምስራቅና ወደ ሌሎች

አገሮች ለመስደድ ሲሞክር በባህር ማበዕልና በበርሃ ሙቀት ሞቶ የሚቀረው ብዙ ነው። ቀንቶት በተባሉት አገሮች የደርሰውም፤ በተለይ ወጣት ሴት እህቶቻችን ስቃይ ሲበዛባቸው ከፎቅ መወርወር እራስን ማጥፋት የተለመደ ሁኗል።

- በወያኔ ዘመን አጠቃላይ የሕዝብ አገልግሎቶች መዳከም ከሀገሪቱ ድህነት ብቻ የሚመነጭ አይደለም። መንግሥት የሕዝብና የአገራዊ ተቋማትን፤ መቆጣጠርና ማስተካከል በሚል የጠባብ አመለካከቱ የተነሳ ሆን ብሎ እንዲዳከሙ ስለሚያደርግ ነው። እናም አገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን አሁን ያለንበት ሁኔታ “አልሞትኩም ብዬ አልዋሺም” የሚለው አባባል የሚስማማን ይመስለናል።